የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፯
አዲስ አበባ - ግንቦት ፳፬ ቀን/፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 47
ADDIS ABABA 1st June, 2007

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፴፰/-፲፱፻፺፱
ስለፌዴራል ታራሚዎች አያያዝ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ..........................................ገጽ ፫ሺ፯፻፯

## CONTENTS

*Council Of Ministers Regulations No.138/2007*

*Council Of Ministers Regulations On The Treatment Of Federal Prisoners..........................................................Page 3707*

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፴፰/፲፱፻፺፱ ስለፌዴራል ታራሚዎች አያያዝ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፯ አንቀጽ ፭ እና በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፭/፲፱፻፺፱ አንቀጽ ፴፱ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ የፌዴራል ታራሚዎች አያያዝ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፴፰/፲፱፻፺፱ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፤

፩. አስተዳደር ማለት የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ነው፤

፪. ማረሚያ ቤት፣ ታራሚ እና የማረሚያ ጠባቂ የሚሉት ቃላቶች በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፫፻፷፭/፲፱፻፺፭ የተሰጣቸው ትርጉም ይኖራቸዋል፤

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 4.85

## *COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS NO.138./ 2007 COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS ON THE TREATMENT OF FEDERAL PRISONERS*

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No 471/2005 and Article 39(1) of the Federal Prison Commission Establishment Proclamation No. 365/ 2003.

1. **Short Title**

These Regulations may be cited as the "Treatment of Federal Prisoners Council of Ministers Regulations No. 138/ 2007".

2. **Definitions**

In these Regulations, unless the context requires otherwise:

1/ "Administration" means the Federal Prisons Administration;

2/ the terms "prison", " prisoner" and "warden" shall have the meanings given to them under the Federal Prisons Administration Commission Establishment Proclamation No. 365/2003;

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O.Box 80001

፫. ፍርድ ቤት ማለት የፌዴራል ፍርድ ቤት ወይም የፌዴራል ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን የተሰጠው ፍርድ ቤት ነው፤

፬. የሕክምና ተቋም ማለት በአስተዳደሩ ሥር የሚገኝ የሕክምና ተቋም ወይም ለማረሚያ ጥበቃ አባላትና ለታራሚዎች የሕክምና አገልግሎት የሚሰጥበት ተቋም ነው::

## ፫. <u>መሠረታዊ መርሆች</u>

የታራሚዎች አያያዝ በሚከተሉት መሠረታዊ መርሆዎች ላይ የተመሠረተ ይሆናል፤

፩. በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በብሔር ብሔረሰብ አባልነት፣ በማህበራዊ ደረጃ ወይም በዜግነት ምክንያት ልዩነት ያለማድረግ፤

፪. የተላለፈባቸው ቅጣት የሚጥለው ገደብ ከሌለ በቀር ሰብዓዊ ክብራቸው እንዲጠበቅ ማድረግ፤

፫. የእሥራት ቅጣቱ አፈፃፀም አስተማሪና ገንቢ መሆኑን ማረጋገጥ::

## ፬. <u>ታራሚዎችን ስለመቀበልና ስለመመዝገብ</u>

፩. ማንኛውም ማረሚያ ቤት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች መሟላታቸውን በማረጋገጥ በፍርድ ቤት ትእዛዝ የሚላኩትን ታራሚዎች ይቀበላል::

፪. ወደ ማንኛውም ማረሚያ ቤት የሚገቡ ታራሚዎች አስተዳደሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በመዝገብ ላይ እንዲመዘገቡና እያንዳንዱ ታራሚ የግል ማህደር እንዲኖረው ይደረጋል::

፫. ማንኛውም ታራሚ ማረሚያ ቤት በሚገባበት እለት የጤና ምርመራ ይደረግለታል::

፬. ታራሚዎች በማረሚያ ቤት ቆይታቸው ስለሚኖራቸው መብትና ግዴታ ይገለጽላቸዋል::

## ፭. <u>ታራሚዎችን ለይቶ ስለመያዝ</u>

፩. ወንድና ሴት ታራሚዎች ተለይተው መያዝ አለባቸው:: በተለይም፣

ሀ/ ለሴት ታራሚዎች የተመደበው ክፍል በጥብቅ መከለል ይኖርበታል፣

ለ/ ሴት ታራሚዎችን የሚጠብቁና የሚቆጣጠሩት ሴት የጥበቃ አባሎችና ኃላፊዎች ብቻ ይሆናሉ፤ ሆኖም የማረሚያ ቤቱ ወንድ የጥበቃ አባላት በተለይም ሐኪሞችና መምህራን በሴቶች ክልል ሙያዊ ተግባራቸውን ማካሄድ ይችላሉ::

፪. የሞት ቅጣት የተወሰነባቸው ታራሚዎች ከሌሎች ታራሚዎች ተለይተው መያዝ አለባቸው::

፫. ሁኔታዎች በፈቀዱ መጠን፣

ሀ እድሜያቸው ከ፲፰ አመት በታች የሆኑ ታራሚዎች ከአዋቂዎች ተለይተው ይያዛሉ፤

ለ ያልተፈረደባቸው ታራሚዎች ከተፈረደባቸው ታራሚዎች ተለይተው ይያዛሉ፤

ሐ ከባድ የወንጀል ሪከርድ ያለባቸው፣ ተደጋጋሚ የወንጀል ድርጊት የፈጸሙና ምግባረ ብልሹ ታራሚዎች ከሌሎች ታራሚዎች ተለይተው ይያዛሉ፤

3/ "court" means a federal court or a court that is entrusted with the judicial authorities of a federal court;

4/ "medical institution" means a health center that function under the Administration or any institution that provide health services for prison wardens and prisoners.

## 3. <u>Basic Principles</u>

The treatment of prisoners shall be based on the basic principles of:

1/ no discrimination on grounds of gender, language religion, political opinion, nation/ nationality, social status or citizenship;

2/ respect to their human dignity unless restricted by the penalties imposed on them;

3/ ensuring that the executions of penalties are educative and rehabilitative.

## 4. <u>Admitting and Registering Prisoners</u>

1/ Any prison shall admit prisoners sent to it by court orders by ascertaining the relevant information.

2/ Prisoners admitted by any prison shall be registered in a registration book and a personal file shall be kept for every prisoner in accordance with directives issued by the Administration.

3/ Any prisoner shall be subjected to medical examinations when admitted to a prison.

4/ Prisoners shall be informed of their rights and duties during their stay in a prison.

## 5. <u>Separate Accommodations of Prisoners</u>

1/ Separate premises shall be allocated for male and female prisoners; particularly,

a) premises allocated for female prisoners shall be securely guarded; and

b) female prisoners shall be guarded and supervised only by female wardens and officials; provided, however, that male wardens, especially medical officers and teachers may carryout their professional duties in the premises set aside for female prisoners.

2/ prisoners on death roll shall be separately accommodated from other prisoners,

3/ To the extent that circumstances allow:

a) juvenile prisoners under the age of 18 shall have separate accommodations;

b) persons detained upon judicial remand shall have separate accommodations from convicted prisoners;

c) prisoners with records of serious crimes, recidivists and indecent prisoners shall have separate accommodations from other prisoners;

መ ተላላፊ በሽታና የአእምሮ ሕመም ያለባቸው ታራሚዎች ከሌሎች ታራሚዎች ተለይ ተው ይያዛሉ::

፬. የታራሚዎችን ማህበራዊና ተሃድሶ ሁኔታ ለማሳካት ይቻል ዘንድ በሚመሳሰሉባቸውና በሚለያዩባቸው ሁኔታዎች በመለየት ሥራ ላይ እንዲሰማሩ ይደረጋል::

፮. **የታራሚዎች ክፍሎች ማሟላት ስለሚኖርባቸው ሁኔታዎች**

ታራሚዎች የሚኖሩባቸውም ሆነ የሚሠሩባቸው ክፍሎች፣

፩. መጽሐፍ ለማንበብ የሚያስችል በቂ ብርሃንና ለጤንነት ተስማሚ የሆነ አየር የሚያስገቡ መስኮቶች፣ እና

፪. በሌሊት መጽሐፍ ለማንበብ የሚያስችል የዐይንን ጤንነት የማይጐዳ መብራት፣ ያሏቸው መሆን ይኖርባቸዋል::

፯. **ስለልብስ**

፩. ማንኛውም ታራሚ በማረሚያ ቤቱ የተዘጋጀውን ልብስ መልበስ አለበት::

፪. በጤና ምክንያት ሐኪም ካዘዘ ወይም አስተዳዳሩ ከፈቀደ ተጨማሪ ልብስ ለታራሚ ሊሰጥ ይችላል::

፰. **ስለመኝታ**

፩. ማንኛውም ታራሚ አስፈላጊ የሆነውን መኝታና የመኝታ ልብስ እንዲያገኝ ይደረጋል::

፪. በጤና ምክንያት ሐኪም ካዘዘ ወይም አስተዳዳሩ ከፈቀደ ተጨማሪ መኝታና የመኝታ ልብስ ለታራሚ ሊሰጥ ይችላል::

፱. **ስለጽዳት**

ታራሚዎች በየጊዜው ንጽሕናቸውን የሚጠብቁበት በቂ ውሃና የንጽሕና መጠበቂያ ቁሳቁስ እንዲሁም የመጸዳጃ ቤት እንዲኖራቸው ይደረጋል::

፲. **ስለምግብ**

፩. ማንኛውም ታራሚ ለጤንነት የሚስማማና የተመጣጠነ በቂ ምግብ በማረሚያ ቤቱ ይቀርብለታል::

፪. በሕመም ምክንያት ሐኪም ካዘዘ ለታራሚው ልዩ ምግብ ይቀርብለታል::

፫. ማንኛውም ታራሚ በቂና ንፁህ የመጠጥ ውሃ ይቀርብለታል::

፲፩. **ስለ ህክምና**

፩. ታራሚዎች ነፃ የህክምና አገልግሎት የማ ግኘት መብት አላቸው::

፪. ማንኛውም ማረሚያ ቤት አቅም በፈቀደ መጠን የህክምና መስጫ ጣቢያ፣ የተሟሉ የህክምና መሳሪያዎች፣ መድሃኒቶችና የህክ ምና ባለሙያዎች ይኖሩታል::

፫. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም፣ ማንኛውም መድሃኒት የህክምና ኃላፊ ካልፈቀደ በስተቀር ወደ ማረሚያ ቤት እንዲገባ ወይም ታራሚዎች እንዲጠቀሙበት አይደረግም::

d) prisoners with communicable diseases and mental cases shall have separate accommodations from other prisoners.

4/ To facilitate the social rehabilitation of prisoners, they shall be categorized on the basis of their similarities and differences and be given different work assignments.

6. **Conditions of Premises**

Premises in which prisoners live or work shall have:

1/ windows large enough to allow adequate light for reading and fresh air to circulate;

2/ adequate artificial light for reading during the night without causing hazard to the eyesight.

7. **Clothing**

1/ Every prisoner shall wear clothes provided by the prison.

2/ A prisoner shall be provided with additional clothes when recommended by a medical officer due to health conditions or when the Administration so permits.

8. **Bedding**

1/ Every prisoner shall be provided with the necessary bed and bedding.

2/ A prisoner shall be provided with additional bed and bedding when recommended by a medical officer due to health conditions or when permitted by the Administration.

9. **Sanitation**

Prisoners shall be regularly provided with enough water and necessary materials for cleanliness and with toilet facilities.

10. **Food**

1/ Every prisoner shall be provided with balanced and sufficient diet by the prison.

2/ Prisoners with health problems shall be provided with special food at the recommendation of a medical officer.

3/ Sufficient and clean drinking water shall be made available for every prisoner.

11. **Medical Services**

1/ prisoners shall be provided with medical treatment free of charge.

2/ to the extent that circumstances allow, every prison shall have a medical facility, adequate medical equipment, pharmaceuticals and medical officers.

3/ Notwithstanding the provisions of sub-article (2) of this Article, any medical drug may not be brought into a prison or dispensed to prisoners without the approval of a medical officer.

፬. ማንኛውም የህክምና ኃላፊ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማንኛውም ታራሚ ወደ ሌላ የህክምና ተቋም ተልኮ እንዲታከም ሃሳብ ያቀርባል:: ማረሚያ ቤቱም ከሃኪሙ በቀረበው ሃሳብ መሠረት ታራሚው ወደ ሌላ ህክምና ተቋም ተዛውሮ እንዲታከም ያደርጋል::

፭. የማረሚያ ቤቱ የንጽህና ሁኔታና የምግቡ የጥራት ደረጃ በህክምና ኃላፊ ቁጥጥር ይደረግበታል:: መስተካከል የሚገባው ካለም የህክምና ኃላፊ እያጠና ለአስተዳደሩ ሃሳብ ያቀርባል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል::

፮. ማንኛውም የህክምና ኃላፊ የዲስፒሊን ቅጣት የተወሰነበት ታራሚ ቅጣቱ ለጤንነቱ ጎጂ መሆኑን ካረጋገጠ ቅጣቱ እንዲቀነስለት ወይም እንዲቀርለት ለማረሚያ ቤቱ ሃሳብ ያቀርባል::

፯. ነፍሰ ጡር የሆነች ታራሚ የመውለጃ ቀኗ ሲደርስ በተቻለ መጠን በቂ የህክምና አገልግሎት ወደሚገኝበት ተቋም ተወስዳ እንድትወልድ ይደረጋል:: ሆኖም ህፃኑ በማረሚያ ቤቱ ውስጥ የተወለደ ከሆነ ይኸው ሁኔታ በልደት የምስክር ወረቀቱ ላይ አይጠቀስም::

፲፪. ስለነፍሰጡርና እመጫት ታራሚ ሴት

፩. ሴት ታራሚ እድሜው ፲፰ ወር ያልበለጠው ሕፃን ይዛ ከመጣችና ለልጁ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ሕፃኑ በማረሚያ ቤቱ ውስጥ ከእናቱ ጋር እንዲቆይ ይደረጋል::

፪. ሕፃኑ በማረሚያ ቤት ቆይታው አስፈላጊውን ምግብ፣ ክትባት፣ ሕክምና እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን እንዲያገኝ ይደረጋል::

፫. ሕፃኑ በማረሚያ ቤት በመቆየቱ በአካሉ ወይም በሥነ ልቦናው ችግር የሚያመጣበት ሆኖ ሲገኝ ለቅርብ ዘመድ እንዲሰጥ ይደረጋል:: ሆኖም የቅርብ ዘመድ የማይገኝ ከሆነ ሕፃኑ ሌላ አሳዳጊ የሚያገኝበትን ሁኔታ አስተዳደሩ ያመቻቻል::

፬. ነፍሰ ጡር ወይም እመጫት የሆነች ታራሚ በሀኪም ትዕዛዝ ተጨማሪ ምግብ እንድታገኝ ይደረጋል::

፲፫. ከጐብኝዎች ጋር ስለሚደረግ ግንኙነት

፩. ታራሚዎች ከትዳር ጓደኞቻቸው፣ ከቅርብ ዘመዶቻቸው፣ ጓደኞቻቸው፣ ከሐኪሞቻቸው፣ ከሕግ አማካሪዎቻቸውና ከሃይማኖት አባቶቻ ቸው ጋር የመገናኘት መብት ይኖራቸዋል:: ዝርዝር አፈፃፀሙ አስተዳደሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል::

4/ A medical officer shall recommend the referral of any prisoner to another medical institution where he finds it necessary for further treatment.

The prison shall transfer such prisoner to another medical institution in accordance with the recommendation of the medical officer.

5/ The sanitation of any prison and quality standards of its food shall be inspected by a medical officer. The medical officer shall undertake studies and recommend to the Administration to take such corrective measures as may be required, and monitor the execution of same.

6/ Any medical officer shall recommend to the prison that a disciplinary penalty imposed on a prisoner be reduced or terminated if he ascertains that the penalty is harmful to the health of the prisoner.

7/ A pregnant prisoner shall, to the extent possible, be taken to a medical institution with adequate facilities at the time of her delivery; provided, however, that if the child is born in the prison, such fact may not be mentioned in the birth certificate of the child.

12. **Pregnant and Female Prisoners with Children**

1/ Where a female prisoner comes with an infant not more than 18 months old and where his interest so requires, the infant shall stay in the prison with his mother.

2/ The infant shall, during his stay in the prison, be provided with the necessary food, vaccination, medical care as well as other necessary items.

3/ If the stay of the child in the prison is likely to have an adverse physical or psychological impact on him, he shall be handed over to a close relative; provided, however, that the Administration shall facilitate the possibilities of finding another guardian in the absence of a close relative.

4/ A pregnant or a female prisoner with a child shall be provided with additional food upon the recommendation of a medical officer.

13. **Communicating with Visitors**

1/ Prisoners shall have the right to communicate with their spouses, close relatives and friends, medical officers, legal counselors and religious fathers. Details shall be determined by a directive to be issued by the administration.

፪. የውጭ ዜጋ የሆነ ታራሚ በአገሩ ኤምባሲ ወይም ቆንሲላ እንዲጐበኝ ይፈቀድለታል::

፲፬. ጐብኝዎችን ስለመፈተሽ

፩. ታራሚዎችን ለመጠየቅ ወደ ማረሚያ ቤት የሚመጣ ማንኛውም ጐብኝ መታወቂያውን በማሳየት በተመሳሳይ ፆታ በማረሚያ ጠባቂ ተፈትሾ እንዲጐበኝ ይደረጋል::

፪. ማንኛውም ጐብኝ እንዲፈተሽ ተጠይቆ ፈቃደኛ ካልሆነ ታራሚዎችን እንዲጐበኝ አይፈቀድለትም::

፫. ማንኛውም ጐብኚ ታራሚዎችን ጐብኝቶ ሲወጣ መፈተሽ ይኖርበታል

፲፭. ጐብኝና ታራሚዎችን ስለመቆጣጠር

፩. ታራሚዎች ከጐብኝዎቻቸው ጋር በሚነጋገሩበት ጊዜ ለጥበቃ ሥራ ተቃራኒ የሆነ ተግባር እንዳይፈጸም ቁጥጥርና ክትትል ይደረጋል::

፪. ማንኛውም ታራሚ ከሕግ አማካሪው ወይም ከጠበቃው ወይም ማረሚያ ቤቱን ለመቆጣጠር ሥልጣን ከተሰጠው ኃላፊ ጋር ግንኙነት ሲያደርግ በማረሚያ ጠባቂዎች እይታ ሥር ሆኖ ንግግሩን በማያዳምጡበት ሁኔታ ይካሄዳል::

፲፮. ታራሚዎችን ስለሚጠይቁ ሕፃናት

እድሜው ከዘጠኝ አመት በታች የሆነ ማንኛውም ሕፃን ከአዋቂ ሰው ጋር ካልሆነ በስተቀር ታራሚን እንዲጠይቅ አይፈቀድለትም::

፲፯. ታራሚዎች በአንድ ቦታ በሕብረት እንዲጐበኙ ስለማድረግ

ታራሚዎች በየክፍላቸው እንዲጐበኙ ለማድረግ አመቺ ባልሆነ ጊዜ የማረሚያ ቤቱ ኃላፊ ሲፈቅድ በአንድ ቦታ በሕብረት እንዲጐበኙ ሊደረግ ይችላል::

፲፰. ስለመፃፃፍ

ታራሚዎች ከማረሚያ ቤቱ ውጭ ካሉ ሰዎች ጋር መጻጻፍ ይፈቀድላቸዋል:: ሆኖም ለጥበቃ ሥራ ተቃራኒ የሆነ ተግባር እንዳይፈጸም በጽሑፎቹ ላይ ቁጥጥር ይደረጋል::

፲፱. ስለ ዝውውር ጥያቄ

ማንኛውም ታራሚ የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ ከሆነና በሌላ ክስ የማይፈለግ ከሆነ ቤተሰቦቹ በሚኖሩበት አካባቢ ወደሚገኝ ማረሚያ ቤት እንዲዛወር ካመለከተ ሊፈቀድለት ይችላል:: ቤተሰቦቹም እንዲያውቁት ይደረጋል::

፳. ስለፖሊስ ምርመራና የፍርድ ቤት መጥሪያ

፩. የፍርድ ቤት ትእዛዝ የያዘ ፖሊስ ወደ ማረሚያ ቤት በመግባት ታራሚን መመር መር ይችላል::

2/ A prisoner who is a foreign national shall be allowed to be visited by the embassy or consular representative of his country.

14. Searching Visitors

1/ Any visitor that comes to a prison to visit prisoners shall show his identification card and go through a body search by a warden of same sex.

2/ Any visitor who refuses to submit for body search may not be allowed to visit prisoners.

3/ Any visitor shall go through a body search after having visited prisoners.

15. Inspecting Visitors and Prisoners

1/ Discussions of prisoners and visitors shall be monitored so as to prevent any action contrary to the custody of prisoners.

2/ Conversations between a prisoner and his legal counselor or attorney or an official authorized to inspect the prison shall be conducted under the surveillance of wardens, but the conversation may not be listened to by same.

16. Children Visiting Prisoners

A child below the age of 9 may not be allowed to visit prisoners unless he is accompanied by an adult.

17. Visiting Prisoners in a Common Place

Where visiting prisoners in their premises is not convenient, they shall be visited in a common place with the permission of the prison administration.

18. Correspondence

Prisoners shall be allowed to correspond with persons outside of the prison; provided, however, that the correspondence shall be inspected to prevent any action contrary to the custody of prisoners.

19. Request for Transfer

Any prisoner who is serving a final sentence and there is no other pending case against him may, upon his request, be transferred to a prison situated in the locality where his relatives reside.

20. Police Investigation and Court Summons

1/ A police officer with a court order may enter into a prison and investigate a prisoner.

፪. ማንኛውም ሰው ማረሚያ ቤቱ ሲፈቅድ በሥራ ሰዓት ወደ ማረሚያ ቤት በመግባት ለታራሚ የፍርድ ቤት መጥሪያ መስጠት ይችላል::

፳፩. <u>የታራሚን ሞት ስለማሳወቅ</u>

ማረሚያ ቤቱ በሞት የተለየ ታራሚ ሲኖር፣

፩. የሞተበትን ምክንያት ከነሐኪም ማስረጃው ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ያሳውቃል፤

፪. ታራሚው መሞቱን ለቤተሰቡ ወይም ለዘመዱ ያሳውቃል፤ አስከሬኑንም ለቤተሰቡ ወይም ለዘመዱ ይሰጣል:: ሆኖም የሚቹን አስከሬን የሚወስድ ቤተሰብ ወይም ዘመድ ካልተገኘ በሚመለከተው ማዘጋጃ ቤት አማካይነት እንዲቀበር ይደረጋል::

፳፪. <u>ስለኑዛዜ</u>

ማንኛውም ታራሚ ኑዛዜ ለማድረግ ሲጠይቅ ማረሚያ ቤቱ አስፈላጊው ሁኔታ እንዲመቻችለት ያደርጋል::

፳፫. <u>ስለትምህርትና ሥልጠና</u>

፩. ታራሚዎች የቀለም ትምህርትና ልዩ ልዩ የሙያ ሥልጠና እንዲከታተሉ ይደረጋል:: ሆኖም ማንበብና መፃፍ የማይችሉ ታራሚዎች እንዲማሩ ቅድሚያ ይሰጣቸዋል::

፪. የትምህርትና ሥልጠና አሰጣጡ ሥልጣን ባለው አካል በወጣው ሥርአተ ትምህርት መሠረት ይሆናል::

፫. ማንኛውንም ትምህርት ወይም ሥልጠና የሚከታተሉ ታራሚዎች ሥልጣን በተሰጠው አካል እውቅና ያለው ፈተና ተፈትነው ካለፉ የትምህርት ማስረጃ ይሰጣቸዋል::

፬. ሴትና ወጣት ታራሚዎች የትምህርት እድል እንዲያገኙ ልዩ ትኩረት ይደረጋል::

፳፬. <u>ስለሰውነት ማጠንከሪያ ትምህርትና መዝናኛ</u>

፩. ማንኛውም ማረሚያ ቤት ታራሚዎች አስፈላጊና ተስማሚ የሆነ የሰውነት ማጠንከሪያ ትምህርትና እንቅስቃሴ እንዲያገኙ ያደርጋል::

፪. ማረሚያ ቤቱ ታራሚዎች በተለያዩ የተሃድሶና የመዝናኛ እንቅስቃሴዎች እንዲሳተፉ ለማስቻል የሚያስፈልገውን ዝግጅት ያሟላል::

፳፭. <u>ስለምክር አገልግሎት</u>

ታራሚዎች በማረሚያ ቤት የቆይታ ጊዜያቸው የባህሪ ለውጥ በማምጣት እሥራታቸውን ጨርሰው ሲወጡና ከሕብረተሰቡ ሲቀላቀሉ ሕግ አክባሪና አምራች ዜጋ እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን የምክር አገልግሎት በባለሙያ እንዲያገኙ ይደረጋል::

2/ Any person may, upon the permission of the prison administration and during working hours, enter into a prison and deliver court summon to a prisoner.

21. **<u>Notifying the Death of a Prisoner</u>**

Where a prisoner dies the prison shall notify the death:

1/ to the competent court together with explanation of the cause of death and submit a medical certificate thereof;

2/ to his family or relatives and hand over the body to them; provided, however, that where there is no family or relative to receive the body, it shall be buried by the municipality concerned.

22. **<u>Wills</u>**

Where a prisoner requests to make a will, the prison shall facilitate all the necessary conditions.

23. **<u>Education and Training</u>**

1/ Prisoners shall be provided with the opportunity to attend academic and different vocational training classes; provided, however, that priority shall be given to illiterate prisoners.

2/ The education and training program shall be conducted in accordance with the curriculum approved by the competent body.

3/ Where prisoners attending academic or vocational training classes pass examinations acknowledged by the competent body, they shall be issued with certificates of qualification.

4/ Particular attention shall be paid to give educational opportunities to female and juvenile prisoners.

24. **<u>Physical Exercises and Recreation</u>**

1/ Any prison shall provide prisoners with the necessary and conducive physical education and exercises.

2/ The prison shall make the necessary arrangements to allow prisoners to participate in different rehabilitation and recreational activities.

25. **<u>Counseling Service</u>**

Professional counseling service shall be provided to prisoners during their stay in prison to bring about behavioral change so that they can become law abiding and productive citizens after their release.

**፳፮. ስለእምነት ነፃነት**

፩. ማንኛውም ታራሚ በማረሚያ ቤት የቆይታ ጊዜው የእምነት ነፃነቱ የተጠበቀ ነው::

፪. የአንድ ታራሚ ሃይማኖት ወደ ማረሚያ ቤት ሲገባ ያስመዘገበው ሃይማኖት ይሆናል:: ሆኖም በማረሚያ ቤቱ ቆይታ ጊዜው ሃይማኖቱን ከለወጠ ይህንኑ ማስመዝገብ ይችላል::

፫. ማንኛውም ታራሚ መንፈሳዊ መጻሕፍቶችን፣ መጽሔቶችንና ጽሁፎችን የማግኘትና የማንበብ እንዲሁም መንፈሳዊ በዓላትን የማክበር መብት ይኖረዋል::

**፳፯. መረጃ የማግኘት መብት**

፩. ማንኛውም ታራሚ ወደ ማረሚያ ቤት በሚገባበት ጊዜ የማረሚያ ቤቱ የስነ ሥርዓት ደንቦች በቃል ወይም በፁሁፍ ይገለፅለታል::

፪. ታራሚው አንብቦ መረዳት የማይችል ከሆነ መረጃው በተሟላ አኳኋን በሚገባው ቋንቋ በቃል ይገለፅለታል::

**፳፰. አቤቱታ የማቅረብ መብት**

፩. ማንኛውም ታራሚ በጽሁፍ ወይም በቃል ደረጃውን ጠብቆ አቤቱታ የማቅረብ መብት ይኖረዋል::

፪. ታራሚው የሚያቀርበው አቤቱታ በአስቸኳይ ውሳኔ አግኝቶ ውጤቱ ለታራሚው ይነገረዋል::

፫. በተሰጠው ውሳኔ የማይስማማ ከሆነ ቅሬታውን ለሚመለከተው ኃላፊ የማቅረብ መብት አለው::

**፳፱. ስለ ታራሚዎች ግዴታ**

ታራሚዎች ስለ ጥበቃ ሥራ፣ ስለሥነ-ሥርዓት አከባበር፣ ስለጽዳት፣ ስለጤና አጠባበቅ፣ ስለማህበራዊ ግንኙነትና ስለሌሎች ጉዳዮች የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን የማክበር ግዴታ አለባቸው::

**፴. ስለ ሥራ አመዳደብ**

፩. ታራሚዎች እንደየሥራ ችሎታቸው፣ ሙያቸውና ጠባያቸው እየታየ የሥራ ደረጃ ወጥቶላቸው እንዲሠሩ ይደረጋል፣ ለሚሠሩት ሥራም ክፍያ ይከፈላቸዋል::

፪. ታራሚው በቂ ችሎታ የሌለው ከሆነ ልምምድ እንዲያደርግና አስፈላጊ ትምህርት እንዲሠጠው ይደረጋል::

**፴፩. እንዲሠሩ ስለማይገደዱ ታራሚዎች**

፩. የዚህ ደንብ አንቀጽ ፴፪ ድንጋጌ ቢኖርም፣

ሀ/ የሞት ፍርድ የተፈረደባቸው ሰዎች፣

ለ/ ሴት ታራሚዎች ከእርግዝናቸው ከ፮ ወር ጀምሮ እንዲሁም ከወለዱ በኋላ እስከ ፪ ወር ድረስ፣

**26. Freedom of Religion**

1/ Every prisoner shall exercise his religious freedom during his stay in prison.

2/ The religion of a prisoner shall be the religion registered at the time of his admission to the prison; provided, however, that if, during his stay in prison, he is converted to another religion, he may request such fact to be registered.

3/ Every prisoner shall have the right to have access to and read spiritual books, magazines and articles as well as to observe religious holidays.

**27. Access to Information**

1/ Rules and regulations of a prison shall be explained orally or in writing to every prisoner on his admission.

2/ Where the prisoner is illiterate the information shall be fully explained to him orally in the language he understands.

**28. Right of Grievance**

1/ Every prisoner shall have the right to lodge a complaint orally or in writing.

2/ Immediate decision shall be made on the complaint of a prisoner and it shall be communicated to him.

3/ The prisoner shall have the right to submit his grievance to the official concerned where he is dissatisfied with the decision.

**29. Obligation of Prisoners**

Prisoners shall have the obligation to observe rules and directives to be issued on custody, discipline, sanitation, health care, social life and other issues.

**30. Work Assignments**

1/ Prisoners shall be categorized and be given work assignments on the basis of their skills, professions and attitudes; and they shall be paid for the work they perform.

2/ Where a prisoner lacks in proper skills, he shall be given the necessary apprenticeship and training.

**31. Prisoners not Compelled to Work**

1/ Notwithstanding the provisions of Article 32 of these Regulations, the following prisoners may not be compelled to work:

a) Persons under death sentence;

b) Female prisoners after the 6th month of their pregnancy and until two months after their delivery;

ሐ/ እድሜአቸው ከ፷ አመት በላይ የሆኑ ወንድ ታራሚዎችና ከ፶ አመት በላይ የሆኑ ሴት ታራሚዎች፣ እና

መ/ በቀጠሮ ላይ ያሉ ሰዎች፣ እንዲሠሩ አይገደዱም::

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩(ለ)፣ (ሐ) እና (መ) የተጠቀሱት ሰዎች ለመሥራት እንደማይገደዱ ተገልጾላቸው ለመሥራት ከጠየቁ ሥራው ጤንነታቸውን የሚጐዳ ካልሆነ በስተቀር ከመስራት አይከለከሉም::

## ፴፪. መሟላት ስለሚገባቸው ሁኔታዎች

፩. ታራሚዎች ለሥራ የሚሠማሩት፣

ሀ/ የሥራው ሁኔታ ለጥበቃ አመቺ መሆኑ ሲታመን፣ እና

ለ/ የጤና ሁኔታቸው አስተማማኝ መሆኑን የህክምና ሀላፊው ሲያረጋግጥ፣ ይሆናል::

፪. ማንኛውም ታራሚ ጎጂ በሆነና ጭካኔ በተሞላበት አኳኋን እንዲሁም በቀን ከ፯ ሰዓትና በሣምንት ከ፮ ቀናት የበለጠ እንዲሠራ አይደረግም::

## ፴፫. ያለክፍያ ስለሚሠራ ሥራ

፩. ታራሚዎች በግል ወይም በቡድን ተደራጅተው ለታራሚዎች ጥቅምና ማህበራዊ አገልግሎት የሚሰሩትን ሥራ አስተዳደሩ ያበረታታል፣ ድጋፍ ይሰጣል::

፪. ታራሚዎች በጋራ የሚገለገሉበትን ማንኛውም ሥራ ያለክፍያ የመስራት ግዴታ አለባቸው::

## ፴፬. ከማረሚያ ቤት ውጭ ስለመሥራት

፩. ፍርደኛ ታራሚዎች ከማረሚያ ቤት ወጥተው እንዲሰሩ አይፈቀድላቸውም::

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ቢኖርም ማረሚያ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ታራሚው ከማረሚያ ቤት ወጥቶ እንዲሠራ ሊፈቀድለት ይችላል:: የክፍያ አፈፃፀሙም በአካባቢው የገበያ ዋጋ ላይ ተመስርቶ ማረሚያ ቤቱ በሚያደርገው ስምምነት መሠረት ይወሰናል::

፫. ታራሚዎች ከማረሚያ ቤት ወጥተው በመሥራት ከሚያገኙት ገቢ ላይ ለማረሚያ ቤቱ ስለሚከፈልበት ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል::

## ፴፭. ገንዘብ ስለማስቀመጥ

ማንኛውም ታራሚ የሚያገኘው ገንዘብ በስሙ የተመዘገበ ደረሰኝ እየተሰጠው በማረሚያ ቤቱ ወይም ለበለጠ ጥንቃቄ አመቺ በሆነ ስፍራ ሊቀመጥ ይችላል:: ካስቀመጠው ገንዘብ ላይ እንዲሰጠው ሲጠይቅም ይከፈለዋል::

c) Male prisoners above the age of 60 and female prisoners above the age of 50; and

d) Persons detained upon judicial remand.

2/ Where persons referred to under sub-article 1(b), (c) and (d) request to work after having been told that they are not compelled to work, they may not be prohibited from working unless the work is hazardous to their health.

## 32. Conditions to be Fulfilled

1/ Prisoners shall be made to work where:

a) The work is believed to be convenient for the custody of the prisoners; and

b) A medical officer ascertains that the prisoners are in good conditions of health.

2/ No prisoner may work under harmful and cruel conditions, nor may he work for more than 7 hours a day and 6 days in a week.

## 33. Works Performed without Payment

1/ The Administration shall encourage and support activities to be performed by prisoners individually or organized in-groups for their benefits and social services.

2/ Prisoners shall have the obligation to perform, without payment, works involving their own common benefits.

## 34. Working outside of Prison

1/ No convicted prisoner shall be allowed to work out side prison.

2. Notwithstanding the provisions of sub article one of this article, the prison may allow a prisoner to work out side prison where it finds its necessary. The amount of payment shall be determined in accordance with agreements entered into by the prison based on the market price of the locality.

3/ Conditions of payment to be made by prisoners to a prison out of their incomes earned by working outside of the prison shall be determined by directives.

## 35. Deposit of Money

The money earned by a prisoner shall be deposited with the prison against a receipt issued in his name or may be deposited in another place for better safe keeping; and payment shall be made out of the deposited money where he requests for it.

**፴፮. የዲሲፕሊን ቅጣት አይነቶች አመዳደብ፣**

፩. የዲሲፕሊን ጉድለት የፈፀመ ታራሚ እንደ ጥፋቱ ክብደት ከሚከተሉት አንዱ ሊወሰንበት ይችላል::

ሀ. ለብቻው ወይም በታራሚዎች ፊት የቃል ማስጠንቀቂያ መስጠት፣

ለ. ከአንድ ወር ላልበለጠ ጊዜ በጐብኚዎች እንዳይጐበኝ ወይም ደብዳቤ እንዳይልክና እንዳይቀበል ወይም ወደ ቤተመጻሕፍት እንዳይገባ ወይም በአንድነት ከሚደረግ ዝግጅትና መዝናኛ እንዳይካፈል መከልከል፣

ሐ. ከስምንት ቀን ላላነሰ ከሁለት ወር ላልበለጠ ጊዜ ለብቻው ለይቶ ማሰር፣

መ. ከአንድ ወር ላላነሰና ከአራት ወር ላልበለጠ ጊዜ በፊደል ተራ /ለ/ ከተዘረዘሩት የቅጣት አይነቶች በአንዱ መቅጣት፣

ሠ. ከሁለት ወር ላላነሰ ከአራት ወር ላልበለጠ ጊዜ ለብቻው ለይቶ ማሰር፣

ረ. ከሚያገኘው የጉልበት ዋጋ ክፍያ አንድ ሶስተኛ ከ፮ ወር ላልበለጠ ጊዜ በመቀነስ ለማረሚያ ቤቱ ገቢ እንዲሆን ማድረግ፣

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ከፊደል ተራ /ሀ/ እስከ /ሐ/ የተዘረዘሩት ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣቶች፣ ከፊደል ተራ /መ/ እስከ /ረ/ የተሠሩት ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣቶች ተብለው ይመደባሉ::

**፴፯. ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች**

የሚከተሉት ጥፋቶች ቀላል የዲሲፕሊን ቅጣት ሊያስከትሉ ይችላሉ::

፩. በሥራ ላይ መለገም፣
፪. ሰንፍና፣
፫. ግዴለሽነት፣
፬. ሣይታመሙ ታምሚያለሁ ብሎ መተኛት፣
፭. ችልተኝነት፣
፮. እምቢተኛነት ማሳየት፣
፯. በማንኛውም ሰው ላይ በአጋጣሚ ወይም በድንገት የእጅ እልፊት ተግባር መፈፀም፣
፰. ከሰው ጋር እንዳይገናኝ ከተከለከለ ታራሚ ጋር ያለ ፈቃድ መገናኘት፣
፱. ያለ ፈቃድ ከመኝታ ክፍል መውጣት፣
፲. ያለ ፈቃድ ከሥራ ቦታ መነሳት፣
፲፩. ያለ ፈቃድ መገኘት ከሚገባው ቦታ ሣይገኝ መቅረት፣
፲፪. የሐሰት አቤቱታ ማቅረብ፣
፲፫. በማንኛውም መንገድ ፀጥታ መንሳት፣
፲፬. ቁማር መጫወት፣
፲፭. ከተወሰነ ቦታ ውጪ መጸዳዳት፣

**36. Types and classification of Disciplinary penalties.**

1/ Depending on the gravity of the of the offence one of the following penalties may be imposed on a prisoner for breach of discipline;

(a) Oral warning in the presence of prisoners or alone,

(b) Prohibiting, for not more than one month from being visited, sending and receiving letter, entering to libraries and participating in joint festive as well as recreational activities,

(c) Solitary confinement for not less than eight days and for not more than two months,

(d) Imposing the penalties specified under paragraph /b/ hereof for not less than one month and for not more than for four months,

(e) Solitary confinement for not less than two months and for not more than four months,

(f) Depending one third of his wages for not more than six months and transferring it to the account of the prison,

2/ The penalties specified under paragraphs /a/ - /c/ of sub article /1/ of this article shall be classified as simple disciplinary penalties; and those specified under paragraphs/d/ - /f/ shall be classified as rigorous penalties,

**37. Offences Entailing simple penalties**

Simple disciplinary penalties may be imposed for the following offences;

1. Tardiness,
2. Laziness,
3. Indifference,
4. Sleeping saying that he is ill while in fact he is not ill,
5. Negligence,
6. Disobedience,
7. Commit un intentional assault on any person
8. Communicating with out permission with a prisoner not allowed to communicate with persons
9. Gating out of bed room with out permission
10. Leaving work place with out permission
11. Not being present, with out permission at a place where he should be present
12. Lodging false petition
13. Disturbing order in any manner
14. Gambling
15. Excreting out side the place intended for the purpose

፲፮. የታራሚዎችን ክፍል ወይም የማረሚያ ቤቱን ቅጥር ግቢ ማቆሸሽ፣

፲፯. በማረሚያ ቤቱ ቅጥር ግቢም ሆነ ከማረሚያ ቤቱ ውጪ መለመን እና

፲፰. ክብደታቸው ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ጋር የሚመጣጠን የዲሲፕሊን ጥፋቶች መፈፀም፣

**፴፰. ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት የሚያስከትሉ ጥፋቶች**

የሚከተሉት ጥፋቶች ከባድ የዲሲፕሊን ቅጣት ሊያስከትሉ ይችላሉ::

፩. አድማ ማድረግ፣ ወይም አድማ እንዲደረግ ማነሳሳት፣

፪. ሁከት ወይም ሽብር መፍጠር፣

፫. ከማረሚያ ቤት ለማምለጥ መሞከር ወይም ማምለጥ፣

፬. ተደጋጋሚ መጥፎ ፀባይ ማሳየት፣

፭. ራስን የማጥፋት ሙከራ ማድረግ፣

፮. የተከለከሉ ነገሮችን ወደ ማረሚያ ቤት ማስገባት ወይም መስጠት ወይም መቀበል፣

፯. መደለያ መስጠት ወይም መቀበል፣

፰. ስርቆት፣

፱. በሀሰት መመስከር ወይም መክሰስ፣

፲. ዝሙት መፈፀም፣

፲፩. በንብረት ላይ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ፣

፲፪. ከባድ የሆነ የእጅ እልፊት መፈፀም፣

፲፫. የኃይል ተግባር መፈፀም ወይም በድርጊቱ መካፈል፣

፲፬. የአስተዳደሩን ወይም የማረሚያ ቤቱን ኃላፊዎች፣ ሠራተኞችና የጥበቃ አባሎች መስደብ፣ ዛቻ፣ በንግግር፣ በተግባር ወይም በሌላ አኳኋን ለመልካም ፀባይ ተቃራኒ የሆነ ተግባር መፈፀም እና

፲፭. ክብደታቸው ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ጋር የሚመጣጠን የዲሲፕሊን ጥፋቶች መፈፀም፤

**፴፱. ስለዲስፕሊን ቅጣት አወሳሰን**

፩. የዲሲፕሊን ጥፋት በፈፀሙ ታራሚዎች ላይ ማረሚያ ቤቱ በዚህ ደንብ መሠረት ተገቢውን የዲስፕሊን ቅጣት ሊወስን ይችላል::

፪. ማንኛውም የዲስፕሊን ቅጣት ከመወሰኑ በፊት ታራሚው ፈጸመ የተባለው ጥፋት ተገልጾለት መልስ እንዲሰጥበት እድል ይሰጠዋል::

፫. የዲስፕሊን እርምጃ ለታራሚ የሚገለጸው በጽሁፍ ሆኖ የይግባኝ እድሉን ጭምር የሚያመለክት መሆን አለበት::

16. Making dirty the rooms of prisoners or the prison premises
17. Beg in side or out side the prison premises and,
18. Commit any breach of discipline of equal gravity with the offences specified herein above.

**38. Offences entailing rigorous penalties**

Rigorous disciplinary penalties may be imposed for the following offences;

1. Conspiring or instigating conspiracy
2. Creating disturbance or terror
3. An attempt to escape or escaping from prison
4. Persistent miss conduct,
5. An attempt to commit suicide,
6. Bring into prison or giving or receiving prohibited things,
7. Giving or receiving bribe,
8. Theft,
9. Perjury or lodging false accusation,
10. Commit adultery,
11. Causing damage to property intentionally or negligently,
12. Commit grave assault,
13. Commit or participating in violence,
14. Insulting, intimidating the administration or prison officials, employees and prison warden or commit in words or in action activities contrary to good conduct in any other manner, and
15. Commit any breach of discipline of equal gravity with the offences specified herein above.

**39. Disciplinary Penalties**

1/ The prison may, in accordance with these regulations, impose appropriate penalties on prisoners, who committed disciplinary offence,

2/ Before any disciplinary measure is taken against a prisoner, he shall be notified of the alleged offence and be given the opportunity to be heard.

3/ Any disciplinary measure shall be disclosed to a prisoner in writing and shall include a statement referring to the prisoner's right to appeal.

**፵. በታራሚ ስለሚፈፀም ወንጀል**

ማንኛውም ታራሚ በማረሚያ ቤት ቆይታው የወንጀል ድርጊት ቢፈጽም ወይም ከማረሚያ ቤት ቢጠፋ በወንጀል ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**፵፩. ባመለጡ ታራሚዎች ላይ ስለሚወሰድ እርምጃ**

፩. ከማረሚያ ቤት ያመለጠ ታራሚ በፈጸመው የማምለጥ ወንጀል ጉዳዩ በፖሊስ ተጣርቶ ክስ እንዲመሠረትበት ይደረጋል፡፡

፪. ታራሚው ከማምለጡ በፊት ከነበረበት የሥራ መደብ ዝቅ ባለ የሥራ ደረጃ እንዲመደብ ይደረጋል፡፡ የማምለጡ ጉዳይም በማረሚያ ቤቱ ተመዝግቦ ይያዛል፡፡

፫. ታራሚው ከማረሚያ ቤት አምልጦ ውጭ የቆየበት ጊዜ ሲፈጸም ከነበረው ቅጣት ላይ ቅናሽ አይደረግለትም፡፡

**፵፪. በታራሚዎች ላይ ስለሚጣሉ ቅጣቶች አፈጻጸም**

ማንኛውም ታራሚ የእስራት ቅጣት በመፈፀም ላይ እያለ በሌላ የወንጀል ጥፋት ምክንያት የቅጣት ውሳኔ ከተላለፈበት የተጣለበት የእስራት ቅጣት የሚፈፀመው የመጀመሪያው ቅጣት ከተፈፀመ በኋላ ነው፡፡

**፵፫. ስለቅጣት መጀመሪያና መጨረሻ ጊዜ**

፩. የእሥራት ቅጣት ጊዜ የሚጀመረውና የሚፈፀመው ቅጣቱን የወሰነው ፍርድ ቤት በሰጠው ትእዛዝ መሰረት ይሆናል፡፡

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም ታራሚው በአመክሮ፣ በይቅርታ ወይም በምህረት ከእሥር ሊፈታ ይችላል፡፡

**፵፬. ስለማረሚያ ቤቱ ግዴታ**

፩. ማንኛውም ታራሚ የእሥራት ጊዜውን ሲጨርስ፣ ይቅርታ ወይም ምህረት ሲያገኝ ወይም ፍርድ ቤት በአመክሮ እንዲፈታ ትዛዝ ሲሰጥ ማረሚያ ቤቱ ታራሚውን ወዲያው የመፍታት ግዴታ አለበት፡፡

፪. ታራሚዎች የእስራት ጊዜያቸውን ሲፈጽሙ መፈታት እንዲችሉ የሚመለከታቸውን ኃላፊዎች የግል ማህደሮቻቸውን በየጊዜው መመርመር አለባቸው፡፡

**፵፭. ስለእስራት ቅናሽ**

፩. ታራሚው የእሥራት ቅናሽ ተደርጎለት እንደሆነ ቅናሹ የሚደረገው በጠቅላላው ከተፈረደበት የእሥራት ጊዜ ላይ ይሆናል፡፡

፪. ታራሚው በገንዘብና በእሥራት እንዲቀጣ ሲፈረድበት ወይም ገንዘቡን መክፈል ባለመቻሉ የእሥራት ቅጣት ሲፈረድበት ቅናሽ የሚደረገው በማረሚያ ቤቱ እንዲፈጸም ከታዘዘው ቅጣት ላይ ብቻ ነው፡፡

፫. በማንኛውም የሕክምና ተቋም ገብቶ በመታከም ላይ የሚገኝ ታራሚ በማረሚያ ቤት እንዳለ ይቆጠራል፡፡

**40. Offence Committed by Prisoners**

Any prisoner who commits a criminal offence while in custody or escapes from prison shall be liable under criminal laws.

**41. Measures taken against Prisoners after having escaped**

1/ A prisoner who escapes from the prison shall be charged with criminal offence based on police investigation.

2/ Such prisoner shall be demoted to a work position lower than the position he occupied prior to his escape. A statement of the fact of escaping shall be entered in a register kept by the prison.

3/ The time the prisoner spent outside of the prison may not be deducted from the term of his sentence.

**42. Execution of Penalties Imposed on Prisoners**

Where a prisoner serving a term of sentence is convicted and sentenced for another offence, the prison term of the latter sentence shall begin after the completion of the prison term of the former sentence.

**43. Beginning and Ending of Term of Sentence**

1/ The term of a sentence shall begin and end in accordance with the order of the court which passed the sentence.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the prisoner may be released upon parole, pardon or amnesty.

**44. Obligation of Prison**

1/ A prison shall have the obligation to immediately release a prisoner upon the completion of the term of his sentence or where he has been granted pardon or amnesty or where the court gives order to release him on parole.

2/ The concerned officials shall periodically check the personal files of prisoners so that they shall be released on the completion of the terms of their sentences.

**45. Reduction of Imprisonment**

1/ Where a term of imprisonment of a prisoner is reduced, the deduction shall be made from the general sentence passed on him.

2/ Where an imprisonment and fine is imposed on a prisoner or where he is sentenced to imprisonment due to his inability to pay a fine, the deduction shall be made from the penalty he has to serve in prison.

3/ The time a prisoner spent in a medical institution for medical treatment shall be deemed to have been spent in a prison.

፬. ታራሚው ወደ ማረሚያ ቤት ሲገባ የእሥራት ቅናሽ ሊያገኝ የሚችልበት ሁኔታ ይገለጽለታል።

፭. በማንኛውም ምክንያት የእሥራት ቅናሽ እንዲያገኝ በሚደረግበት ጊዜ አስተዳደሩ ታራሚው እንዲያውቀው ማድረግ አለበት።

፮. በታራሚው ላይ የተጣለበት ቅጣት፣ የተፈቀደለት ወይም የተከለከለው የእሥራት ቅናሽ እና የእሥራቱ ዘመን የሚያልቀበት ጊዜ በግል ማህደሩ ተመዝግቦ ይቀመጣል።

**፵፮. <u>አመክሮ ስለሚጠየቅላቸው ታራሚዎች</u>**

ማንኛውም ታራሚ፣

፩. በማረሚያ ቤት መልካም ጠባይ ካሳየ፣

፪. ከተፈታ በኋላ መልካም ውጤት ሊያስገኝ ይችላል ተብሎ ከተገመተ፣

፫. በፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረት የሚፈለግበትን ማንኛውንም ክፍያ አጠናቅቆ ከፈጸመ፣

፬. ሁለት ሦስተኛውን የእሥራት ቅጣት ከፈጸመ ወይም የእድሜ ልክ እሥራት ተፈርዶበት ሃያ አመት ከታሠረ፣ እና

፭. ለማሕበራዊ ኑሮ መልካም ዝንባሌ የሚያሳይ ከሆነ፣ አመክሮ ይጠየቅለ ታል።

**፵፯. <u>የአመክሮ ኮሚቴ ስለማቋቋም</u>**

፩. በአመክሮ ሊፈቱ የሚችሉ ታራሚዎችን ጉዳይ የሚያጠና አንድ ሰብሳቢና አራት አባላት ያሉት ኮሚቴ ይቋቋማል።

፪. ኮሚቴው የሚያቀርበው ሃሣብ በማረሚያ ቤቱ ዋና አስተዳዳሪ ጸድቆ ለመጨረሻ ውሣኔ አግባብ ላለው ፍርድ ቤት ይቀርባል።

**፵፰. <u>ይቅርታ ስለሚጠየቅላቸው ታራሚዎች</u>**

ታራሚዎች በማይድን ሕመም፣ በእድሜ መግፋት ወይም በማረሚያ ቤት ቆይታቸው በሚያሳዩት የባህሪ ለውጥ ምክንያት ይቅርታ ሊጠየቅላቸው ይችላል።

**፵፱. <u>ታራሚዎች ከእሥር ሲፈቱ ሊሟሉ ስለሚገባቸው ሁኔታዎች</u>**

፩. ማንኛውም ታራሚ በአመክሮ፣ በይቅርታ፣ በምሀረት ወይም የእሥራት ጊዜውን ጨርሶ ከእሥር ሲፈታ በማረሚያ ቤት ያስቀመጠውን ገንዘብ፣ ልብስ ወይም ዕቃ ካለ ደረሰኝ ፈርሞ ይወስዳል ወይም ለሚወክለው ሰው ወይም ድርጅት ይሰጥለታል።

፪. ታራሚው ሲፈታ ገንዘብ የሌለው መሆኑ ከተጣራ በኋላ ወደ ቀድሞ መኖሪያ ቦታው ለመመለስ የሚያስችለው ለመጓጓዣና ለስንቅ የሚሆን ገንዘብና ልብስ ማረሚያ ቤቱ ይሰጠዋል።

፫. ማንኛውም ታራሚ ከእሥር ሲፈታ ማረሚያ ቤቱ ከእሥር የተፈታ መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል።

4/ A prisoner shall, when admitted to a prison, be provided with information on conditions that may entitle him to the reduction of the term of his imprisonment.

5/ The Administration shall inform a prisoner when his sentence is reduced on any ground.

6/ The sentence passed on a prisoner, the granting or denial of reduction of his sentence and the date of completion of sentence shall be recorded in his personal file.

**46. <u>Prisoners Eligible for Parole Request</u>**

Parole shall be requested for a prisoner who:

1/ behave well during his imprisonment;

2/ is believed to be commendable after his release;

3/ has settled all payments required under a court decision;

4/ has already served two-thirds of the term of his sentence or 20 years of his life sentence; and

5/ has positive inclination towards social life.

**47. <u>Parole Committee</u>**

1/ A committee consisting of a chairperson and four members shall be established to study cases of prisoners that may be released on parole.

2/ The recommendations of the Committee shall, upon the endorsement of the chief administrator of the prison, be submitted to the appropriate court for its final decision.

**48. <u>Prisoners Eligible for Pardon Request</u>**

Pardon may be requested for prisoners on grounds of incurable diseases, old age or behavioral change during their stay in prison.

**49. <u>Conditions to be Fulfilled upon Release of Prisoners</u>**

1/ Where a prisoner is released on parole, pardon or amnesty or upon completion of his term of sentence, he shall, upon signing a receipt, receive his money, clothes or goods, if any, deposited with the prison or he may authorize a person or an organization to receive same on his behalf.

2/ Where, through investigation, it is ascertained that a prisoner, at the time of release, has no money, the prison shall provide him with clothes and money to cover his transportation and subsistence costs to travel to his former residence.

3/ Every prisoner shall, upon his release, be provided with a certificate of release issued by the prison.

፶ **የታራሚዎች መዝገብ ስለማቋቋም**

የታራሚዎች የሕይወት ታሪክና ቅጣት የሚመዘገብበት መዝገብ ይቋቋማል፡፡

፶፩. **መመሪያ ስለማውጣት**

አስተዳደሩ ይህን ደንብ በአግባቡ ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል፡፡

፶፪. **ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ደንቦችና መመሪያዎች**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

፶፫. **ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር

50. **Register of Prisoners**

A register of prisoners shall be established to record the personal histories and penalties of prisoners.

51. **Power to Issue Directives**

The Administration may issue directives necessary for the proper implementation of these Regulations.

52. **Inapplicable Regulations and Directives**

No regulations or directives shall, in so far as they are inconsistent with these Regulations, be applicable with respect to matters covered by these Regulations.

53. **Effective Date**

These regulations shall enter into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 23rd day of July 2007.

*MELE ZENAWI*

*PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC*

*REPUBLIC OF ETHIOPIA*